# በኑሮ መሻሻል የተገለፀ እድገት

አዲስ ቶልቻ 03/01/14

ኢትዮጵያ በዓለም ዘንድ ስምዋ ከኢኮኖሚ ዕድገት ጋር ተያይዞ መነሳት ከጀመረ አንድ አስርት ዓመት አስቆጠረ። ከዚያ በፊት የዓለም የመገናኛ ብዙሃን፣ በአፍሪካ በተለይ በኢትዮጵያ ላይ የሚሰሩ ጥናቶች፣ ዓለም አቀፍ የፋይናንስ ተቋማት የሚያወጧቸው ሪፖርቶች ኢትዮጵያን በረሃብና ጦርነት ገፅታዋ ነበር የሚገልጿት። ኢትዮጵያ ለዓለም ስታሳይ የኖረችው ገፅታዋ ረሃብ ፣ ድህነትና ጦርነት ነበር።

አሁን ግን ይህ ተቀይሯል፡፡ በኢኮኖሚና በማህበራዊ ልማት፣ በሰላምና መረጋጋት፣ ለአፍሪካና ለምስራቅ አፍሪካ ቀጠና በምታበረክተው የሰላም ማስከበርና ትብብር የምትጠቀስ አገር ለመሆን በቅታለች፡፡ ባለፉት አስርት አመታት ባስመዘገበችው እድገት ዙሪያ አንድም በኢትዮጵያ ውስጥ እድገት አልታየም ብሎ በይፋ የካደ ዓለም አቀፍ የገንዘብ ተቋም የለም፡፡

በዚህ እድገት ዙሪያ ልዩነት ቢኖር እንኳ የእድገቱ መጠን ላይ እንጂ እድገት አለ የለም የሚለው ላይ አይደለም፡፡ የኢትዮጵያ መንግስት በአማካይ ባለሁለት አሃዝ የኢኮኖሚ ዕድገት ማስመዝገቡንና ይህንን የማስቀጠል ዕቅድ እንዳለው ሲገልፅ፣ ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ተቋማት ደግሞ "የለም እድገታችሁ ከ7 በመቶ አይበልጥም" የሚል ልዩነት ነበር ሲስተዋል የቆየው። ይህንንም ቢሆን መጨረሻ ላይ የተቀበሉበት ሁኔታ ተሰተውሏል፡፡

ለምሳሌ የዓለም ባንክ ባለፈው አመት መግቢያ ላይ ባወጣው ሪፖርት ኢትዮጵያ በለፉት አስር አመታት በአማካይ ከ10 በመቶ በላይ እድገት ማስመዝገቧን፣ ይህም ከሳህራ በታች ካሉ አገራት ከተመዘገበው 5 በመቶ አማካይ እድገት ጋር ሲነፃፀር ከፍተኛ መሆኑን ገልጦ እንደነበረ ይታወሳል። ይህን ተከትሎ ለአራት አመታት የሚቆይ አዲስ የአጋርነት ስትራቴጂ ነድፎ የ4 ቢሊየን ዶላር ድጋፍ ማደረጉም ይታወቃል፡፡

በሌላ በኩል በተመሳሳይ ወቅት  ዓለም አቀፉ የገንዘብ ድርጅት (አይ ኤም ኤፍ) ኢትዮጵያን በተመለከተ የመግባቢያ (consultation) ሰነድ  ባፀደቀበት ወቅት ባወጣው ሪፖርት “በ2003 እና በ2004 7 በመቶ የኢኮኖሚ እድገት ተመዝግቧል፣ ይህ መሰረተ ሰፊ እድገት ቀጣይነት ይኖረዋል፣ በተወሰዱ የድህነት ቅነሳ እርምጃዎች በ2002/2003 የነበረውን 38.7 በመቶ የድህነት መጠን ወደ 29.6 በመቶ እንዲቀንስ ማድረግ ተችሏል” ብሏል፡፡  እነዚህ በዓለም አቀፍ የፋይናንስ ተቋማት የተሰጡ ምስክርነቶች ኢትዮጵያ ውስጥ ሊካድ የማይችል እድገት መመዝገቡን ያረጋግጣሉ፡፡

ለነገሩ ምንም አይነት የኢኮኖሚ ሙያዊ ትንታኔዎች ሳይኖሩም ኢትዮጵያ ያስመዘገበችውን የአኮኖሚ ዕድገት ለመረዳት ይቻላል። የተመዘገበው እድገት  በሕዝቡ ኑሮ ላይ በግልፅ የሚታይ መሻሻል ያስከተለ በመሆኑ ነው  ከሙያዊ አስረጂ ውጭም እድገቱን መረዳት ይቻላል ያልኩት።

የአገሪቱ የኢኮኖሚ መሰረት የሆነውና 80 በመቶ ያህል ሕዝብ በተሰማራበት በግብርናው ዘርፍ የታየው እድገት በአርሶ አደሩ የኑሮ ደረጃ መሻሻል በተጨባጭ ታይቷል። ከ10 ዓመታት በፊት የኢትዮጵያ አርሶ አደር፣ ስኳርና የምግብ ዘይት የመሳሰሉ መሰረታዊ የፍጆታ ምርቶች ተጠቃሚ አልነበረም። እነዚህን የፍጆታ ምርቶች ተጠቀመ ከተባለ ምርት በሚሰበሰብበት ወር ጥርና የካቲት አንድ ሰሞን ብቻ ነው። ለከተሜዎች ብቻ የተተዉ ሸቀጦች ነበር የሚመስሉት፡፡ አሁን ግን ይህ ታሪክ ሆኗል። የኢትዮጵያ አርሶ አደር በፊት ቅንጦት ይመስሉት የነበሩትን ስኳር፣ የምግብ ዘይትና መሰል ምርቶች የዘወትር ፍጆታው ለማድረግ በቅቷል።

በአርሶ አደሩ መኖሪያ ቤት፤ አልጋ፣ ወንበር፣ ጠረጴዛ፣ ቴፕ ሪከርደር የመሳሰሉ የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሳቁሶችን ከተማ እንግድነት ሲሄድ የሚያያቸው ለከተሜዎች ብቻ የተፈቀዱ ብርቅ እቃዎች አድርጎ ነበር የሚወስዳቸው፡፡ አሁን ግን የአርሶ አደሩ ቤት ገብተዋል። ከዚህ በተጨማሪ በእያንዳንዱ አርሶ አደር ቤት ቢያንስ አንድ ተንቀሳቃሽ ስልክ አለ፡፡ ገመድ አልባ ስልክ ተጠቃሚ አርሶ አደሮችም አሉ፡፡ ቦላሌ መታጠቅ፣ ኰትና

ጃክት መደረብ፣ ጫማ መጫማት ለአር አደሩ ያልተፈቀዱ ነበር የሚመስሉት፡፡ አሁን ግን የዘውትር አልባሳቱ ለመሆን በቅተዋል፡፡

አርሶ አደሩ በሳር ክዳን ቤት ውስጥ እንዲኖር የተፈጠረ ነበር የሚመስለው። በአርሶ አደሩ መንደር የቆርቆሮ ቤት ማየት ብርቅ ነበር። በገጠር የቆርቆሮ ክዳን ቤት አልፎ አልፎ የሚታይ በመሆኑ ለቦታ ማመልከቻነት ያገለግል ነበር። አሁን ግን ይህ ተለውጧል። አርሶ አደሩ ደረጃውን የጠበቀ የቆርቆሮ ክዳን ቤት ውስጥ መኖር ከጀመረ ከራርሟል። አሁን አሁን ቀድመው የነበሩ ሁኔታዎች ተገልብጠው የሳር ክዳን ቤት ብርቅ ወደመሆን እየተሸጋገረ ነው።

የኢትዮጵያ አርሶ አደር ድሮ መኪናን የሚያውቀው ከተማ ለገበያ ሲሄድ አቧራ አስነስቶ በአጠገቡ ሲያልፍ ነበር። በመኪና ተሳፍሮ መጓዝ ለአርሶ አደሩ ወግ ነበር። አሁን ግን ይህ ሁሉ ተቀይሮ አርሶ አደሩ የጭነት ካምዮኖች ባለቤት ለመሆን የበቃበት ደረጃ ላይ ደርሷል። አሁን በአንድ የአርሶ አደር ቀበሌ ቢያንስ አራትና አምስት የጭነትና የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ባለቤት ለመሆን የበቁ አርሶ አደሮች አሉ። ለግል መጓጓዣ ሞተር ሳይክል የሚጠቀሙ አርሶ አደሮች ቁጥርም ቀላል አይደለም፡፡

በርካታ አርሶ አደሮች በከተማዎች የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ ባለሶስት ጎማ ተሽከርካሪዎች (ባጃጅ) ባለቤት ለመሆን በቅተዋል። ምርታማነቱን ለማሳደግ ለመስኖ ልማት የሚጠቀሙበት የውሃ ፓምፕ ያላቸው አርሶ አደሮችም በርካቶች ናቸው። በከተሞች የሚከራዩ የመኖሪያ ቤቶች ያገነቡም አሉ።

አሁን አርሶ አደሩ ልጆቹን ያስተምራል። ከብት ጥበቃ የአርሶ አደሩ ልጅ እጣ ፈንታ የሆነበት ግዜ ታሪክ ሆኗል፡፡ የመንግስት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት (ዩኒቨርሲቲና ኮሌጆች) ገብተው የመማር እድል ያላገኙትን ልጆቹን ደግሞ የግል ዩኒቨርሲቲና ኮሌጆች ገንዘቡን ከፍሎ ያስተምራል። ይህን የማድረግ አቅም አለው። አሁን የማይማር የአርሶ አደር ልጅ መመልከት እንግዳ ነገር ነው።

በአጠቃላይ ከላይ ከተገለጠው በተጨማሪ በከተማዎች ትላልቅ ፎቆችን እስከማስገንባት ሌሎች የኢንቨስትመንት ስራዎች ላይ ለመሰማራት የበቁ በርካታ ሚሊየነር አርሶ አደሮች ተፈጥረዋል።እድገቱ አንዳንድ ተቃዋሚዎች እንደሚሉት የሚነገር ብቻ ሳይሆን መሬት ላይ ያለ ነው ማለት ነው፡፡

በከተማ ያለውም ሁኔታ ተመሳሳይ ነው። አዲስ አበባን ጨምሮ ሁሉም የአገሪቱ ከተሞች በመሰረተ ልማት በፈጣን እድገት ላይ ናቸው፡፡ኢትዮጵያ ውስጥ ከርዕሰ መዲናዋ አዲስ አበባ ጋር የሚመጣጠን ለኑሮ አመቺ የሆኑ የመኖሪያ ቤቶች፣ ቢሮዎች፣ የሕክምና መስጫ ተቋማት፣ የትምህርት ተቋማት ያላቸው በርካታ ከተሞች ተፈጥረዋል። አዳማን፣ አዋሳን፣ ባህርዳርን፣ መቀሌን ለአብነት ማንሳት ይቻላል። ድሮ የተሟላ ቁሳዊና መንፈሳዊ ፍላጎቶች የተሟሉበት ሕይወት ለመኖር አዲስ አበባ መኖር የግድ ነበር፡፡ አሁን ይህ ተቀይሯል። ይህ የከተሞች የእድገት ውጤት ነው።

በከተሞች የታየው እድገት የሕንፃና የመሰረተ ልማት ግንባታ፣ የአገልግሎትና የማምረቻ ተቋማትት ኢንቨስትመንቶች በአገሪቱ ታሪክ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ የስራ ዕድል ፈጥረዋል። ከዚህ በተጨማሪ መንግስት ስራ አጥ ወጣቶችን በአነስተኛና ጥቃቅን ተቋማት አደራጅቶ፣ የብድርና የመስሪያ ቦታ በማቅረብ ወደ ስራ እንዲገቡ አድርጓል። በዚህ የአነስተኛና ጥቃቅን ተቋማት ባለፈ ሶስት አመታት ብቻ ከ3 ሚሊየን በላይ ዜጎች የስራ ዕድል አግኝተዋል።

ከሃያ አመታት በፊት የከሙዓለ ሕፃናት እስከ ሁለተኛ ደረጃ የሚያሰተምሩ የግል ትምህርት ቤቶች ቁጥር ከአራትና አምስት አይበልጥም ነበር፣ ለዛውም በአዲስ አበባ ከተማ የተወሰኑ ነበሩ፡፡ ከሃያ አመት በፊት ልጆቻቸውን ከፍተኛ ክፍያ በሚጠይቁት በእነዚህ የግል ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ ከተሜዎች ቁጥርም እጅግ አነስተኛ ነበር፡፡ አሁን የእነዚህ የግል ሙዓለ ሕፃናትና የግል ትምህርት ቤቶች ትምህርት ቁጥር እጅግ በጣም አድጓል፣ በየክለሉ ከተሞችም ይገኛሉ።' የተማሪዎቹም ቁጥር የዛኑ እጅግ በጣም ጨምሯል። ይህ እንዲሆን ያስቻለው የከተሜዎች ገቢ መጨመር ነው፡፡

ይህ ድሮ ያልነበር የአኮኖሚ እድገት በድንገት በአጋጣሚ የተፈጠረ አይደለም። መንግስት የሚከተለው የኢኮኖሚ ልማት ፖሊሲና ዕቅድ ውጤት ነው። የኢፌዴሪ መንግስት ከፍተኛ የኢኮኖሚ እድገት በተመዘገበባቸው ያለፉ አስርት አመታት በየአምስት አመት የተከፋፈለ የልማት ዕቅድ ነድፎ ተግባራዊ ለማድረግ ተንቀሳቅሰስል።

ለምሳሌ ከ1998 እስከ 2002 ተግባራዊ የተደረገው የድህነት ቅነሳና ቀጣይነት ያለው ልማት እቅድ፣ እንዲሁም አሁን በመተግበር ላይ የሚገኘውና ከ2003 እስከ 2007 የሚቆየው የእድገትና የትራንስፎርሜሽን እቅድ ተጠቃሾች ናቸው።

የኢፌዴሪ የሚኒስትሮች ምክር ቤት  የካቲት 14/2006 ዓ/ም ከ2003 እስከ 2007 ተግባራዊ የሚሆነውን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ያለፉ ሶስት አመታት አፈፃፀም ገምግሞ ውሳኔዎችን አሳልፏል።

በዚህ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የሶስት ዓመታት አፈፃፀም ግምገማን ተከትሎ ይፋ የሆነው መግለጫ እንደሚያመለክተው ባለፈው ዓመት፣ ማለትም በ2005 በጀት አመት አመታዊ አጠቃላይ የምርት እድገት 9.7 በመቶ እንደነበረ አስታውቋል። ይህ እድገት በየዘርፉ ያለውን ድርሻ አስመልክቶም ግብርና 7.1 በመቶ፣ ኢንደስትሪ 18.5 በመቶ አገልግሎት 9.9 በመቶ መሆኑን ገልጿል።

የአፍሪካ ሕብረት አባል አገራቱ የምግብ እጥረት ችግርን ለመፍታት ከአመታዊ በጀታቸው ቢያንስ 10 በመቶውን ለግብርና ዘርፍ ልማት እንዲመድቡ ሲወስን አያይዞ የዘርፍ አመታዊ እድገት ቢያንስ 7 በመቶ መሆን እንደሚገባው ማስቀመጡ ይታወሳል። በ2005 ዓ/ም ኢትዮጵያ በግብርናው ዘርፍ ያሳየችው 7.1 በመቶ እድገት ሌሎች የአፍሪካ ሀገራት ገና ሊደርሱበት ያቀዱት በመሆኑ እንደስኬት ሊቆጠር የሚችል ነው።

የሚኒስትሮች ምክር ቤት መግለጫ በ2005 በኢትዮጵያ የተመዘገበውን 9.7 በመቶ አጠቃላይ እድገት አስመልክቶ በእቅድ ከተያዘው ጋር ሲናፃፀር ዝቅ ያለ ቢመስልም ከሳሀራ በታች ያሉ አገራት ካስመዘገቡት የ5 በመቶ አማካይ እድገት ጋር ሲነፃፀር የላቀ ሊባል የሚችል መሆኑን ጠቁሟል። ይህ እድገት በአገር ውስጥና በዓለም አቀፍ ደረጃ

ፈታኝ የገበያ ሁኔታዎች ውስጥ የተገኘ መሆኑንም ውጤቱ ከፍተኛ መሆኑን እንደሚያመለክት ገልጿል።

የአንድ አገር ኢኮኖሚ እያደገ ሲሄድ በሁሉም ዘርፎች ዕድገት መታየቱ የሚያስፈልገውን ያህል በእድገት ውስጥ የተለያዩ ዘርፎች (sectors) የሚኖራቸው ድርሻ መለወጥ ይጠበቅበታል - መዋቅራዊ ለውጥ ያስፈልጋል። በዚሁ መሰረት ኢንደስትሪው በኢኮኖሚው ውስጥ ያለው ድርሻ በአንፃራዊነት የበለጠ እያደገ መሄድ ይጠበቅበታል። በአንፃራዊነት የአገልግሎትና የግብርናው ዘርፍ ድርሻ እየቀነሰ ይመጣል። ይህ ማለት የግብርናውና የአገልግሎት ዘረፎች እድገት አያሳዩም ማለት ሳይሆን ኢንደስትሪው በንፅፅር እጅግ በከፍተኛ መጠን ማደግ ይጠበቅበታል ማለት ነው።

የኢትዮጵያን እድገት ከዚህ አንፃር ሲታይ፣ በእድገትና ትራንስፎሜሽን ግምገማ መሰረት የግብርናው ዘርፍ በ2002 ዓ/ም ከአጠቃላይ የአገሪቱ ምርት ውስጥ የነበረው 46.5 በመቶ ድርሻ ከሶስት አመት በኋላ በ2005 ዓ/ም ወደ 42.9 በመቶ ዝቅ ብሏል። በሌላ በኩል ኢንደስትሪው በ2002 ዓ/ም የነበረው 10.3 በመቶ ድርሻ ወደ 12.4 በመቶ፣ የአገልግሎት ዘርፉ ደግሞ ከ44.1 በመቶ ወደ 45.2 በመቶ ከፍ ብሏል።

የእድገቱ ዋነኛ ምንጭ የሆነውና 80 በመቶ ያህል ሕዝብ የተሰማራበት ግብርና ባለፉት ሶስት አመታት ያሳየው እድገት በግምገማ ሪፖርቱ ላይ በዝርዝር ሰፍሯል። በ2002 ዓ/ም 202.4 ሚሊየን ኩንታል የነበረው የግብርና ምርት በ2005 ዓ/ም ወደ 251.5 ሚሊየን ኩንታል አድጓል ምርታማነትንም በተመለከተ በሄክታር 15.4 ኩንታል የነበረው በ2005 ዓ/ም ወደ 17.82 ኩንታል አድጓል።

የኢኮኖሚ ዕድገት መድረሻው ሰዎች የኑሮ ፍላጎታቸው ተሟልቶ የተሻለ ሕይወት እንዲኖሩ ማስቻል ነው። በሌላ አነጋገር በአገራችን ሁኔታ ዜጎች የተሻለ ሕይወት እንዳይኖሩ አድርጓቸው የነበረውን ድህነት መቀነስ ነው።

በዚህ ረገድ ባለፉት ሶስት የእድገትና የትራንስፎርሜሽን እቅድ አመታት፣ በ2003 ዓ/ም 29.6 በመቶ የነበረው ከድህነት በታች የሚኖር የሕብረተሰብ መጠን በ2005 ወደ 26

በመቶ ዝቅ ማለቱን ሬፖረቱ አመልክታል። ይህን አሃዝ በ2007 ዓ/ም ወደ 22.2 በመቶ ዝቅ ማድረግ እንደሚቻልም የሚኒስትሮች ምክር ቤት ባደረገው የእቅድ አፈፃፀም ግምገማ ማረጋገጡንም አስታውቋል።

የአንድ አገር ዜጎች የተሻለ ሕይወት መኖር የሚለካው በቁሳዊ ኢኮኖሚ ዕድገት ብቻ አይደለም። የማህበራዊ ኑሮ እድገትም ያስፈልገዋል። ከእነዚህ መሃከል ጤናና ትምህርት ትልቅ ቦታ ይሰጣቸዋል። በዚህ ረገድ ባለፉት ሶስት አመታት ትልቅ መሻሻል ተመዝግቧል።

በ2002 በአገሪቱ የነበሩ 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች (ከ1ኛ - 8ኛ ክፍል) 26 ሺህ 951 የነበሩ ሲሆን በሶስት ዓመታት ውስጥ ወደ 34 ሺህ 495 አደገዋል። የተማሪዎች ቁጥርም ከ15 ነጥብ 8 ሚሊዬን ወደ 17.4 ሚሊዬን አድጓል። የ2ኛ ደረጃ ትምህርትን በተመለከተ በ2002 ዓ/ም 1ሺህ 335 የነበሩ ትምህርት ቤቶች በ2005 1ሺህ 912 መድረስ ችለዋል። በከፍተኛ የትምህርት ዘርፍ በግልና በመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች የቅድመ ምረቃ ፕሮግራም ተማሪዎች ቁጥር 553 ሺህ 848 ደርሷል። ይህ እድገት በእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ የተያዘውን ከሁለት ዓመት በፊት አስቀድሞ ማሳካት መቻሉን ያመለክታል።

መንገድ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እድገትን በማፋጠን ረገድ ትልቅ ድርሻ ያለው መሰረተ ልማት ነው። በመሆኑም መንግስት ለመንገድ ልማት ትልቅ ትኩረት ሰጥቷል። በዚህም ከሶስት ዓመት በፊት በ2002 ዓ/ም የነበረው 48 ሺህ 800 ኪሎ ሜትር መንገድ በ2005 ወደ 58 ሺህ 33 8 ኪሎ ሜትር አድጓል።

በጤናም ረገድ ባለፉት ሶስት የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አመታት መልካም ውጤት መገኘቱን ነው ዕቅዱን የገመገመው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ያሳወቀው። የጤና ተቋማት ግንባታ በተመለከተ በ2002 ዓ.ም. 14 ሺህ 192 የነበረው የጤና ኬላ ብዛት በ2005 ዓ.ም. 14 ሺህ 48 መድረሱን አመልክቷል፡፡ የጤና ጣቢያ በ2002 በጀት ዓመት 2 ሺህ 142 የነበረውን በ2005 ዓ.ም. ወደ 3 ሺህ 100 ያደገ በመሆኑ በዘርፉ የተቀመጠውን ስታንዳርድ በአጭር ጊዜ ማሳካት እንደሚቻል የግምገማው ሪፖርት አስታወቋል።

በዚህ ፅሁፍ እንደተመለከተው በኢኮኖሚ እድገት አመላካች አሃዞች የተገለፀ እደገት አንዳንድ ተቃዋሚዎች እንደሚሉት ለፕሮፓጋንዳ ፍጆታነት በመንግስት የሚነገሩ ሳይሆኑ በተጨባጭ በዜጎቸ ኑሮ ላይ መሻሻል የተገለፁ ናቸው፡፡ ዓለም አቀፍ ምስክርነትም አግኝተዋል፡፡